

## ꧁31-2꧂

# ከፍትወት ወጥመድ እንሽሽ

***ለሥጋ መሞት የማያዳግም ድል ያስገኛል***

አንዳንድ ጨርሶ የማይልቁ ጦርነቶች አሉ። ጦርነቱ አንዴ ተፋፍሞ በማለቅ ፈንታ እየተጎተተ ይሄዳል። ይህን የመሰለ ጦርነት መሪውንና ተዋጊዮችን ቀስ በቀስ እያዳከመና እየጎዳ የሚሄድ ነው። ክርስቲያኖችም በማያዳግም ሁኔት ጠላታችንን ወግተን በመጣል ፈንታ በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ እንኖራለን። "ለሥጋዬ ሞቼአለሁ" በማለት እራሳችንን አሳልፈን በመስጠት ፈንታ ሰይጣን እንዲያባብለንና በመደጋገምም በራችንን እንዲያንኳኳ ዕድል እንሰጠዋለን። በዓለም ውስጥ ብዙ የማይዳግሙ ጦርነቶች እንደተካሄዱ ታሪክ ይመሰክራል። የጦርነቱ ድል የማይዳግም በመሆኑ ከዚህ በፊት ያጨቃጭቅና ያጣላ የነበረው ምክንያት የመጨረሻ መልስ ያገኛል። እግዚአብሔር ለእኛም በጾጋው የማይዳግም ድሎችን ሊሰጠን ይችላል። ይህንን ስንል ሌሎች ውጊያዎች ወይንም ጦርነቶች ከዚህ በኋላ አይኖርብንም ማለት አይደለም። ለእግዚአብሔር ልባችንን ሙሉ በሙሉ ባለመስጠታችን "ለሥጋዬ ሞቼአለሁ" ማለት ባለመቻላችን የሕይወታችንን በር ከፍተን በመልቀቃችን ሰይጣን የልባችንን በር እንዲያንኳኳ ዕድል እንሰጠዋለን።

***ኃጢአት ላለመሥራት ውሳኔው የእኛ ነው***

መፈተን ኃጢአት አይደለም። "ፈተና" ኃጢአት እንድንሠራ የሚጠራ ግብዣ ብቻ ነው። ኢየሱስም ተፈትኗል ግን ኃጢአተኛ አልነበረም (ዕብ. 4፥15)። ኢየሱስ ከተፈተነ እኛም እንፈተናለን። ፈተናን ለመግፋት መሞከር እኛን ከመፈተን አያድነንም። መፈተን እንዳይደርስብን መታገል ይበልጥ እራስን መጉዳት ይሆናል። ፈተናው ባለበት ሥፍራ ይሁን። ፈታኙ ለዚያ ፈተና አለመሸነፋችንን ሲያውቅ ጊዜውን ጠብቆ ይሄዳል። ፈተናው ካለበት ሥፍራ ሸሽቶ መሄድ ግን ከመፈተን አያድንም። ፈተና ከሚበዛበትም ሁኔታና አካባቢ እራስን ሆን ብሎ መክተት ደግሞ አላዋቂነት ነው። ሰይጣን ኃይለኛ ነው። እኛን ለመጣል በተለያየ አቅጣጫ ያለማረፍ ይጥራል። ይሁን እንጂ እጃችንን ጠምዝዞ ልክ ያልሆነውን ነገር የማስደረግ ኃይል የለውም። የማድረግ ውሳኔው ያለው በእኛው ውስጥ ብቻ ነው። እራሳችንን ከኃላፊነት ነጻ ካደርግን ግን ድካማችን በየትኛው አቅጣጫ እንደሆነ አውቀን በዚያ በደከምንበት አቅጣጫ እራሳችንን ይበልጥ ለማዘጋጀትና ለማጠናከር አንችልም።

***በሥጋ ፍትወት የተፈተኑ***

***ሀ) ዳዊት በፍትወቱ ተሸነፈ***

በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ውስጥ የነበሩ ዳዊትና ዮሴፍ ተመሳሳይ ፈተና ቀረበላቸው። ሁለቱም ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው ከአምላካቸው ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነትና ኅብረት እንዲኖራቸው የሚጥሩ ወጣቶች ነበሩ። ከእግዚአብሔር በጎ ነገር የተቀበሉ በመሆናቸው ሁለቱም ኃጢአት በመሥራት አምላካቸውን ማሳዘን አይፈልጉም። ዳዊት ለቀረበለት ፈተና ወዲያው እጁን እንዳልሰጠ እርግጠኞች ነን። ከሥጋ ፍትወት ከዓይን አምሮት ጋር ከፍተኛ ግብ ግብ ሳይፈጥር አልቀረም። በተለመደው ዘዴው በሔዋን ላይ እንዳደረገው ሳይጣን የዳዊትን የዓይን መስኮት ከፍቶ ቤርሳቤጥ ገላውና ስትታጠብ አሳየው። "ማማሯን አየህ? ውበቷን

ተመለከትክ የሰውነቷን ቅርጽ ልብ አልክ?" እያለ በዳዊት ስሜት ላይ መጫወት ጀመረ። በዙሪያው የነበሩት የሚስቶቹና የቁባቶቹ ውበት እንዳይታዩት ዓይኑን አሳውሮ በኦርዮን ሚስት በቤርሳቤጥ ላይ ብቻ ዓይኑን እንዲጥል አደረገው። "እግዚአብሔርን አሳዝናለሁ" እንዳይል እግዚአብሔርን አስረሳው። "ከተጋለጥኩ በኃጢአቴ በእሥራኤል ሕዝብ ፊት እዋረዳለሁ" እንዳይል ማንም ሰው እንደማያውቅ ነገሩ ተሸፍኖ እንደሚቀር ዘዴና ብልሃት አሳየው። በመጨረሻ በሥጋ ፍትወቱ ተሸንፎ በዝሙት ወደቀ። ከዚህ በኋላ ያለውን ታሪክ መጥቀሱ የታወቀውን ታሪክ መድገም ይሆናል።

## ለ) ዮሴፍ የሥጋ ፍትወትን አሸነፈ

ዮሴፍ የዳዊትን ዓይነት ፈተና የቀረበለት ወጣት ነው። ዮሴፍ እንደ ዳዊት ራቁቷን የሆነች ሴት አይመልከት እንጂ ከዚያ የበለጠ ፈተና ቀርቦለታል። ዳዊት በሥጋ ፍትወት ምክንያት የወደቀው ተጠይቆ ሳይሆን በስልጣኑ ተጠቅሞ ነበር። እንደ ዘመኑ ቢሆን ኖሮ "አስገድዶ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት" (rape) በማድረጉ ተከስሶ ይፈረድበት ነበር። የዮሴፍ ሁኔታ ግን ይህን የመሰለ አልነበረም። የተለያየ ግብዣ ከጶጢፋር ሚስት ቀርቦለታል።

ሀ) በተለያየ ጊዜ ዮሴፍን እንደምትፈልገው በሰውነቷ፣ በዓይኑ (body language) ገልጻለታለች። ለዮሴፍ ይህ የመጀመሪያ ደርጃ ፈተናው ነበር። ብዙ ክርስቲያኖች የሚወድቁት ገና ከዚህኛው ደርጃ ላይ ሳሉ ነው። ለመውደቅ በቋዋፍ ላይ ያሉ ከሆነ ደግሞ "እንዲህ ማለቷ ወይንም ይህን የመሰለ አመለካከቷ እኔን መፈለጓ ነው" በማለት የተሳሳተ ትርጉም ይዘው ለመታለልና ለመውደቅ ግብ ግብ ይጀምራሉ። ዮሴፍ ግን የጶጢፋር ሚስት ሃሳቧ በግልጽ ቢገባውም በልቡ የሰጠው መልስ "እምቢ" የሚል ነበር።

ለ) "ምናልባት ሁኔታዬን ለዮሴፍ አልገባውም ይሆናል" በማለት አፍ አውጥታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ከእርሱ ጋር ለማድረግ እንደምትፈልግ ገልጻ ጠየቀችው። ዮሴፍ ግን አጥጋቢ ምክንያት በመስጠት "እምቢ! አይሆንም" በማለት የማያዳግም መልስ ሰጣት። ብዙዎች የመጀመሪያውን የፈተና ደረጃ ከቻሉ በሁለተኛ የፈተና ደርጃ ላይ እጃቸውን ይሰጣሉ። ሰይጣን በአእምሮአቸው እንዲጠቀሙ ያደርግና "እንዴት ሴት ልጅ አፍ አውጥታ ስትጠይቅህ "እምቢ" ትላለህ! "እምቢ" ብትላት ስሜቷን ፍጹም ስብርብሩን እንደምታወጣው እወቅ። አንተ ግን ክርስቲያን በመሆንህ ማንም እንዲጎዳ አትፈልግም" ይለዋል። ሰይጣን ዘዴኛ ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ጠቅሶም ያሳየዋል። "ከእነዚህ ከትንንሾቹ አንዱን የሚያስት የወፍጮ መጅ በአንገቱ አሥሮ ወደ ውሃ ውስጥ ቢሰጥም ይሻላል" የሚለውን ጥቅስ በማሳየት "ይህቺ ልጅ አፍራ እንዳትሰናከል መጠንቀቅ አለብህ። ባይሆን እንኳን ፍላጎቷን ከአሟላህ በኋላ ንስሀ መግባት ትችላለህ" ይለዋል። ወገኖቼ ለዚህ የሚያዋጣው መልስ "እምቢ! አላደርገውም" ነው። ከወደቅን በኋላ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ቢሆንም ኃጢአት ዋጋ ያስከፍላልና የማይሽር መጥፎ ጠባሳ ትቶልን እንደሚሄድ አንርሳ።

ሐ) ዮሴፍ ፈተናው እዚህ ላይ አላበቃም። በማያዳግም ሁኔታ ሰይጣንን እራሱን ካልመታው እንደ ማይለቀው ግልጽ ነው። ሰይጣንም ሁሉን የማወቅ ችሎታ ስለሌለው የዮሴፍን ቁርጥ ውሳኔ አልተረዳም ነበር። ስለሆነም፥ የመጨረሻውንና ኃይለኛውን ሙከራ አደረገበት። የጶጢፋር ሚስት በግድ "አብረኸኝ ተኛ" ስትል ልብሱን ጨምድዳ ያዘች። ዮሴፍ የቀርበለት ፈተና ከዚህ ደርጃ ሲደርስ ቀደም ሲል እንዳደርገው የጶጢፋርን ሚስት ንግግር (reason out) በማድረግ ብቻ ሊመልሳት እንደማይችል አወቀ። የነበረው ምርጫ ጨርቁን ጥሎላት መሸሽ ብቻ ነበር። ብዙዎች ከሦስተኛ የፈተና ደረጃ ሲደርሱ ፈታኙን በንግግር በኤቲክስ በፐሪስፐል (ሥርዓተ ፍልስፍና) ለማሳመን ይሞክራሉ። ወገኖቼ እዚህ ላይ ምንም ነገር አይሠራም። አጭሩ መንገድ ጥሎ መሸሽ ብቻ ነው (2 ጢሞ. 2፥22)።

**ጠቃሚ ምክር**

1) የጥቂት ደቂቃ ደስታ የዕድሜ ልክ ውርደት እንደሚያስከትል ምንጊዜም አንርሳ።

2) ያገቡ ወንዶችም ሆነ ሴቶች በሥራ ብዛት በአገልግሎት ብዛት ለኑሮ ጓደኞቻቸውና ለራሳቸው በማሰብ አስፈላጊውን የተቀደሰውን የሥጋ ግንኙነት ከኑሮ ጓደኞቻቸው ጋር ከማድረግ ቸል እንዳይሉ ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ከኑሮ ጓደኞቻቸው የሚፈልጉትን ሲያጡ ፍልጎታቸውን ከውጪ ለማሟላት ስለሚፈልጉ ለፈተና ይጋለጣሉ።

3) እራስችንን ለፈተና አጋልጠን አንስጥ። በተለይ አገልጋይ ለምክር ለማስተማር አብሮ ለመጸለይ ከአንዲት ሴት ጋር ብቻውን ባይሆን መልካም ነው። ቢሆን እንኳን የሚመክርበት ክፍል በሩ ክፍት ይሁን።

4) እህቶቻችን ለማጽናናት በአጉል ሰዓት ወይንም በጨለማና ሰው በሌለበት ወቅት ማድረግ እራስን ለፈተና ማጋለጣ ይሆናል። አንዳንዶች ሲመሽባቸው የግድ እዚያው ለማደር ይገደዳሉ። በዚህ ሁኔታ ሄደው በኃጢአት የወደቁ ብዙ ወንድሞ ጽፈውልኛል።

5) ያለአግባብ ከሥርዓት በወጣ መልክ በተለይ ወንዶች ከተቃራኒ ጾታ ጋር መተቃቀፍ መተሻሸት እራስንና ሌላውን ፈተና ውስጥ መክተት ይሆናልና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

6) ሴቶች እህቶቻችንን "ይህን ልበሱ ያን አትልበሱ ማለት ሕግ አጥባቂነት ቢመስልም፥ የእግዚአብሔር ቃል ሴቶች በሥርዓት እንዲለብሱና እንዲያጌጡ የሚመክር መሆኑ መርሳት የለብንም። እህቶቻችን አለባበሳቸው ወንዶችን ፈተና ውስጥ የሚያስገባቸው እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። "እኔን ደስ ካለኝ ግዴለኝም" ማለት ትክክል አይመስለንም። ስለሌላው ሕይወት ግድ ሊኖረን ይገባል። ብዙ ጊዜ ወንዶች ስለ ሴቶች የተሳሳተ ሃሳብ እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸው አለባበሳቸው ብቻ ሳይሆን አቀራረባቸውም (body language) ጭምር ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

7) በተለይ ከአገር ወደ አገር ከቦታ ወደ ቦታ ብዙ የሚጓዙ ሰዎች ለሥጋ ፍትወት ፈተና በጣም የተጋለጡ ናቸው። ብዙ ጊዜ ለብቻቸው ናቸው። ከኑሮ ጓደኛቸው ያገኙት የነበረው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ተጓድሎባቸዋል። ያሉበት አካባቢ ማንም ስለማያውቃቸው ይበልጥ ለመፈተንና ለመውደቅ አመቺ ሁኔታ ላይ ይሆናሉ።

8) ዓይናችንን እንጠብቅ። የምናነበውን መጽሐፍና መጽሔት እንምረጥ። የምንመለከተው የቴሌቪዥን ፕሮግራም የተመረጠ ይሁን። መገኘት ከማይገባን ሥፍራና አካባቢ እንራቅ።

9) ምላሳችንን እንጠብቅ። የሥጋ ፍትወት መንፈስን የሚያሳይ ቋንቋ አንጠቀም። ለሰሚው ልዩ ትርጉም ከሚሰጥ ንግግር ከማናገር እራሳችንን እንግታ።

10) አዕምሮአችን ሥራ አይፍታ። ሰይጣን ብዙ ጊዜ ሥራውን የሚያካሂደው ሥራ በፈታ አእምሮ ውስጥ ነው። ያለ አንዳች ሥራ ቁጭ ብሎ ማሰብ ለሥጋ ፍትወት ፈተና እርስን አጋልጦ መስጠት ይሆናል።

11) ሳያገቡ አብሮ መኖር እራስን ፈተና ውስጥ መክተት ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖች መጥፎ ምስክርነት ይሆናል።

..............................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እንክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**